የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር OFAGF-03.24/6/15
ቀን 29/06/2015

ለክብርት አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ

የቱሪዝም ሚኒስትር

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የቱሪዝም ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት</u>

<u>ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል</u>

የቱሪዝም ሚኒስቴር የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 14 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 10 ገጽ የሂሣብ ሪፖርቶች በድምሩ 24 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እየገለጽን ለኦዲት ግኝቶች የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት እንድትልኩልን እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አበራ ታደሰ

የፌዴራል ም/ዋና ኦዲተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የቱሪዝም ሚኒስቴር

የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ

ኦዲት ሪፖርት

የካቲት 2015

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የቱሪዝም ሚኒስቴር

የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

የቱሪዝም ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የቱሪዝም ሚኒስቴር ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆን በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የቱሪዝም ሚኒስቴር ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው።

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የቱሪዝም ሚኒስቴር የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የሂሳብ እንቅስቃሴ መዝግብና የሂሳብ ሪፖርት ላይ የታዩ ልዩነት

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመመሪያው መሰረት የሂሳብ ምዝገባ እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- የገቢ ሂሳብ ሰኔ 30/2013 በሂሳብ ሪፖርት ላይ ከሂሳብ መደብ 1451199 ብር 250,778.96 የሚታይ ሲሆን ሰኔ 30/2013 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ 477,546.08 የሚታይ በመሆኑ የገቢ ሂሳብ በብር 226,767.10 በማነስ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤
- ተሰብሳቢ ሂሳብ በሰኔ 30/2013 የሂሳብ ሪፖርት ላይ 1,148,227.60 የሚታይ ሲሆን በሰኔ 30/2013 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ብር 35,401,148.10 የሚታይ በመሆኑ በብር 34,252,920.50 በማነስ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤
- ተከፋይ ሂሳብ በሰኔ 30/2013 የሂሳብ ሪፖርት ላይ 3,167,774.87 የሚታይ ሲሆን በሰኔ 30/2013 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ብር 2,210,544.85 የሚታይ በመሆኑ በብር 957,230.02 በመብለጥ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

2. ያለአግባብ በድጋሚ ለውጭ አገር ጉዞ የአየር ትኬት የተከፈለ ወጪ

የፌደራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግሥት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤት ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ላይ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል::

ይሁን እንጂ መ/ቤቱ በተባበሩት መንግስታት የዓለም ንግድ ድርጅት ከኖቬምበር 28/2021 እስከ ዴሴምበር 05/2021 በ24ኛ ጠቅላላ ጉባኤ በስፔን ማድሪድ ከተማ

እንዲሳተፉ ክብርት ወ/ሮ ሰላማዊት ዳዊት የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዲኤታ፣ ወ/ሮ ለሊሴ ዱጋ የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን ኮሚሽነር እና ወ/ሮ ሮዛ መኮንን ከኢቢሲ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በተፈቀደው መሰረት በቀን 30/06/2014 በወጪ ማስመስከሪ ቁጥር 00000228 በሂሳብ መደብ 2221102 ብር 425,552.00 ለአየር ትኬት ግዥ ክፍያ የተወራረደ ቢሆንም ከላይ የተገለፁት ለሁለቱ የስራ ኃላፊዎችና ለአንድ ኢቢሲ ጋዜጠኛ በቀን ህዳር 26 /2021 ከአዲስ አበባ ማድሪድ የደርሶ መልስ የአየር ትኬት ብር 343,045.00 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም፣

- ለክብርት ወ/ሮ ሰላማዊት ዳዊት እና ለወ/ሮ ለሊሴ ዱጋ ከ29 ኖቬምበር እስከ 05 ዲሴምበር ከማድርድ አዲስ አበባ የመጡበት በሚል የአየር ትኬት ለእያንዳንዳቸው ብር 25,242.00 በድምር ብር 50,484.00 በድጋሚ የተከፈለ መሆኑ፣
- ለወ/ሮ ለሊሴ ዱጋ ህዳር 26/2021 ከማድርድ አዲስ አበባ የመጡበት በሚል በድጋሚ ብር 25,242.00 (2,821 ዶላር) ሌላ የአየር ትኬት የተቆረጠ መሆኑ፣
- በቀን 18/06/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 00000049 ከማድሮድ አዲስ አበባ ለመጡበት በሚል ለክብርት ወ/ሮ ሰላማዊት ዳዊት ብር 25,242.00 እና ለወ/ሮ ለሊሴ ዱጋ ብር 25,242.00 በድምር ብር 50,484.00 ለአየር መንገድ በድጋሚ የተከፈለ መሆኑ፣
- በተጨማሪም ከመስሪያ ቤቱ ዉጪ በስብሳበው የተሳተፉት ወ/ሮ ለሊሴ ዱጋ የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን ኮሚሽነር ብር 145,807.00 እና ለወ/ሮ ሮዛ መኮንን ከኢቢሲ ብር 51,431.00 የደርሶ መልስ የአየር ትኬት ብር 197,238.00 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም የትራንስፖርት ወጪው ከመ/ቤቱ እንዲሸፈን የተፈቀደበት ማስረጃ ሳይኖር ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

በድምር ብር 151,452.00 ለአየር ትኬት በተደጋጋሚ ያለአግባብ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ የዳረገ ከመሆኑ በተጨማሪ በድምር ብር 197,238.00 ከመስሪያ ቤቱ ዉጪ በስብሰባው ለተሳተፉት ለወ/ሮ ለሊሴ ዱጋ እና ወ/ሮ ሮዛ መኮንን የትራንስፖርት ወጪ በመ/ቤቱ እንዲሸፈን የተፈቀደበት ማስረጃ ሳይኖር ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>በወጪ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በቅድመ ክፍያ ተመዝግቦ የተገኘ የወጪ ሂሳብ፡</u>

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው በሂሳብ እንቅስቃሴያቸው መመዝገብ እና ሪፖርት ማቅረብ እንዳለባቸው መመሪያው ይገልጻል:: ይሁን እንጂ መ/ቤቱ የወጪ ሂሳቦችን በትክክለኛው የሂሳብ አርዕስታቸው እየመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡

በድምሩ ብር 1,093,456.46 የተለያዩ የወጪ ሂሳቦች በወጪ መመዝገብ ሲገባው በተሰብሳቢ ሂሳብ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ በመሆኑ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት ዝቅ እና የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርትን ከፍ ብሎ እንዲታይ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

4. <u>ባልተሟላ ማስረጃ የተወራረደ የወጪ ሂሳብ</u>

የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 14 ተራ ቁጥር 4 መሠረት ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት ያዛል፡፡

ይሁን እንጂ የመ/ቤቱ የ2014 በጀት ዓመት ወጪ በድምር 31,659.87 በተለያዩ የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ የተወራረደ ቢሆንም ለወጪው ትክክለኛነት የክፍያ ደረሰኝ ሳይቀርብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

5. <u>ያላግባብ የተከፈ የቅጣት ክፍያ</u>

የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል ሁለት ንዑስ አንቀጽ 6(ሀ) የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች የመስሪያ ቤታቸውን ሥልጣንና ኃላፊነት በመወጣትና የፀደቀውን በጀት መሠረት በማድረግ ወጪዎችን በመፈጸም በኩል መስሪያ ቤታቸውን የመምራትና የሚወከል ፕሮራሞችና መስሪያ ቤታቸውን የሚመለከቱ ህጎች በማስፈጸም በኩል ከፍተኛ ኃለፊነት እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡

- ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመጋቢት 2012 እስከ ጥቅምት 2013 ዓ.ም ድረስ ያለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ፣ ዊዚሆልድ ታክስ ፣ሥራ ግብር እና ጡረታ በወቅቱ ለገቢዎች ሚኒስቴር ክፍያ ባለመፈጸሙ ምክንያት በቀን 29/10/2014

በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 1017530 ቅጣት ብር 90,541.26 ወለድ ብር 78,147.75 በድምር ብር 168,689.01 ቅጣት የከፈለ መሆኑ፤

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ተርሚናል 2 ለሚገኘው የእንግዳ መቀበያ ለተከራየው ቢሮ ኪራይ በቀን 15/06/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 00000178 ከጥቅምት 2014 እስከ ሀምሌ 7 2014 የቤት ኪራይ ብር 431,999.92 ክፍያ ሲፈጽሙ በወቅቱ ባለመክፍሉ ብር 38,061.67 ቅጣት የተከፈለ መሆኑ ፤

በድምሩ ብር 206,750.68 ቅጣት በመክፈል መ/ቤቱን ለተጨማሪ ወጪ የተዳረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

6. **ከመመሪያ ውጭ ለኃላፊ የመኖሪያ ቤት ዕድሳት ያለአግባብ የተፈጸመ ክፍያ፣**

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 2 የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ኃላፊነት ለመወሰን በወጣው አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በኃላፊነታቸው ስር የሚገኘው የመንግስት ሀብት ለተገቢ እና አግባብ ባለው የመንግስት አካል ለጸደቀ ዓላማ ብቻ መዋሉን እንዲሁም አጠቃቀሙ ቁጠባን፣ ብቃትን እና ውጤታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መፈጸሙን የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ በዚህም መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስትን ውስን ሀብት ለታለመለት የመ/ቤቱ ዓላማ ብቻ የሚያውል እና ግዥዎችን በመመሪያው መሰረት የሚያከናውን መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

ለክብርት አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ ከፌደራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የተሰጠው ቤት በቤቶች ኮርፖሬሽን ማደስ ወይም ማስጠገን ሲባው፡-

- በቀን11/4/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0000916 በሂሳብ መደብ 2631101(6412) ቅድመ ክፍያ 30% ብር 129,375.00 እና
- በቀን 18/9/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 497 በሂሳብ መደብ 2241101 ቀሪ ክፍያ ብር 301,875.00 የተከፈለ በመሆኑ፤

በድምሩ ብር 431,250.00 ያለአግባብ ከመመሪያ ውጪ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ወጪ በውስን ጨረታ ለአሸናፊው ድርጅት ሜሮን ማሞ ፍንሽግ ሰርቪስ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

7. <u>ባልተለመደ የሂሳብ ምዝገባ የሚታይ የተጣራ ሀብት</u>

በፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ቁጥር 2 ፊደል ለ መሰረት የእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን ዴቢትና ክሬዲት ጠብቆ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በመመሪያው መሰረት እያንዳንዱ ሂሳብ አርዕስት በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

የመ/ቤቱ የ2014 በጀት ዓመት የተጣራ ሀብት በሂሳብ መደብ 5601(7111101) በድምር ብር 957,230.32 ከመደበኛ የሂሳብ ሚዛን ውጭ በዴቢት የታየ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች የ2014 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርቶች በፋይናንስ አዋጅና ደንብ እንዲሁም በሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት የተከናወነ ባለመሆኑ በእኛ አስተያየት የመሥሪያ ቤቱ የፋይናንስ አቋም የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳይም፡፡

ምንም እንኳን ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸውና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች(Emphasis matter)</u>

1. <u>የተሟላ ዕቃ ገቢ ደረሰኝ /ሞዴል 19 /ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያ፣</u>

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባው ጥንቃቄ ንዑስ አንቀጽ 3 እቃው ወደ መ/ቤቱ ዕቃ መጋዝን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ መ/ቤቱ በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በቀን 30/10/2014 በኢንቮይስ ቁጥር 1568 በሂሳብ 2311101/ 2311102 መደብ አዲስ ለሚከራየው ህንፃ የብር 30,000,000.00 የፈርኒቸር ግዥ ከዕሲያና

ትሬዲንግ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን በቀረበው የንበረት ገቢ ደረሰኝ ላይ የዕቃው ዓይነት እና በቁጥር ያልተገለጸ መሆኑ፤

- በቀን 29/10/2014 በኢንቮይስ ቁጥር 1131 በሂሳብ መደብ 2241103 የማስታወቂያ ህትመት አገልግሎት ግዥ ለመፈፀም ከኢትዮጵያ ፕረስ ድርጅት ብር 460,000.00 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም በንብረት ገቢ ደረሰኙ ላይ ዕቃውን ስለመረከቡ የተረካቢ ፊርማ የሌለው መሆኑ፤

በድምር ብር 30,460,000.00 እቃው ገቢ ለመሆኑ የተሟላ የንብረት ገቢ ደረሰኝ/ሞዴል 19/ ያልቀረበለት በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

2. ያለሂሳብ መደቡ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፤

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው መመሪያው ይገልጻል ። በመሆኑም መ/ቤቱ የወጪ ሂሳቦችን በትክክለኛው የሂሳብ አርዕስታቸው እየመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

በድምሩ ብር 9,067,319.27 ያለሂሳብ አርዕስቱ/መደቡ የተመዘገበ ሂሳብ መኖሩ በኦዲት ታውቋል፡፡

3. ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት በተመለከተ፤

የፌዴራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀፅ 12 ተራ ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛ በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ሆኖም ሚኒስቴሩ መ/ቤቱ የ2014 የበጀት ዓመት አጠቃቀሙን በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ለየፕሮግራሞቹ ከተደለደለው የመደበኛ በጀት ሂሳብ በአግባቡ ስራ ላይ ከዋለው ሂሳብ ጋር ሲነጻጸር በየፕሮግራሙ በተመለከቱት አንዳንድ የወጪ አርዕስቶች ከ10% በላይ ሲታይ፡-በበጀት ዓመቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተደለደለው መደበኛ በጀት በድምሩ ብር 19,361,802.97 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

4. <u>ለኦዲት ያልቀረበ የሂሳብ ሪፖርት እና ማስረጃን በተመለከተ፤</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 የፌደራል ዋና ኦዲተር ሰነዶችና የቃል መረጃዎች ሁሉ ሲጠየቁ የተጠየቀዉ ግለሰብ፣ ሰራተኛ ወይም ባለሥልጣን በትክክልና በተሟላ አኳኋን ወዲያዉኑ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

ይሁን እንጂ መ/ቤቱ ቱሪዝም ሚኒስቴር ከመሆኑ በፊት ቀድሞ ቱሪዝም ኢትዮጵያ በነበረበት ወቅት በድጎማ መልክ ከገንዘብ ሚኒስቴር የተለቀቀለት ብር 40,000,000.00 ቢሆንም የሂሳብ ምዝገባና የሪፖርት ስርዓት የፌዴራል መንግስት የሂሳብ ምዝገባና የሪፖርት ስርዓት ተከትሎ ምዝገባ የማይደረግና ለገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርት የማያቀርብ በመሆኑ ኦዲት ለማድረግ የተስተካከለ የሂሳብ ሪፖርትና የሂሳብ እንቅስቃሴ ምዝገባ ለኦዲት እንዲቀርብ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ሊቀርብ ባለመቻሉ ከሃምሌ 1/2013 ዓ.ም እስከ ጥር ወር 2014 ዓ.ም ድረስ የነበረውን የድጎማ በጀት የሂሳብ እንቅስቃሴና አመዘጋገብ ስርዓት ኦዲት አድርጎ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት አልተቻለም፡፡

<u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)፤</u>

1. <u>የአላቂና ቋሚ ንብረት አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ፤</u>

በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 2 ንብረት አመዘጋገብና አሰተዳደር ፤አንቀጽ 3 የስቶክ አሰተዳደር እንዲሁም አንቀጽ 5 የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ ፣ የመጠቀም ፣ የመቆጣጠር እና አገልገሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንደሚገባ ይገልፃል በዚሁ መሰረት ባለስልጣኑ የንብረት አያያዝ ፣ አጠቃቀም እና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ፡

- የንብረት ምዝገባ ገቢና ወጪ በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤
- በተጠቃሚዎች እጅ ለሚገኙ ንብረቶች ዩዘር ካርድ ያልተዘጋጀ መሆኑና መለያ ቁጥር /ታግ/ ያልተለጠፈባቸው መሆኑ፤
- የቋሚና አላቂ እቃዎች የራሳቸው እስቶር የሌላቸው በመሆኑ እቃዎቹ በአንድ ላይ ተቀላቅለው በአንድ እስቶር ውስጥ የሚገኙ መሆኑና በተጨማሪ በእስቶር ውስጥ የሚገኙ እቃዎች ቢን ካርድ ቢኖራቸውም ወጪና ገቢ በሚሰራበት ጊዜ የማይቀናነስ መሆኑ፤

- በርካታ ቁጥር ያላቸው መፅሂቶችና ደረሰኞች መወገድ ሲኖርባቸው በስቶር ውስጥ ለረዥም ጊዜ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- ፕሪንተር በቁጥር 1፤ዴስክ ቶፕ ኮምፒተሮች በቁጥር 5፤ 55 ኢንች ቴሌቪዥን በቁጥር 1 በብልሽት ምክንያት ለረዥም ግዜ በስቶር ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- አሮጌ ጎማዎች በቁጥር 48፤ ባህላዊ ወንበሮች በቁጥር 4፤ ከተገዙ ከአንድ አመት በላይ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በስቶር ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤
- ሌኖቮ ላፕቶፕ በቁጥር 6 ፤ዴል ላፕቶፕ በቁጥር 1 ጥቅም ላያ መዋል እየቻሉ ለረዥም ጊዜ በንብረት ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

2. <u>የተሽከርካሪዎች አያያዝ፣ አጠባበቅና በተመለከተ፤</u>

የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ሥምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሠረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡

- የ29 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊቢሬ) በሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሥም መሆኑ፤

በሚኒስቴር መ/ቤቱ ውስጥ ያሉ 10 ተሽከርካሪዎች በጋራዥ ለጥገና ተብለው የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

3. <u>የነዳጅን አጠቃቀም በተመለከተ፤</u>

የፌደራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ተራ.ቁ 9.1 መስሪያ ቤቶች የተሽከርክሪዎችን የነዳጅ ፍጆታ ለመከታተልን መዝግቦ ለመያዝ እንዲረዳቸው የተሽከርካሪዎች የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጅ የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው በመከታተል ማረጋገጥ እንዳለባቸው ይገልጻል ይሁን እንጂ፡-

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጥር 9/05/2014 ጀምሮ የጥምቀት በአልን ለማክበር ወደ ጎንደር ሲሄዱ የቱሪዝም ሚኒስቴር ዴኤታ እና አብሯቸው ለሚጓዙት ሹፌር ለአቶ ብርሀኔ ግርማዩ የቀን አበል እና ነዳጅ ከነመጠባበቂያው ብር 16,104.68 ክፍያ የተፈፀመ ሲሆን፤

- ከቀን 10/05/2014 እስከ 15/05/2014 ድረስ በየቀኑ ነዳጅ የተቀዳ መሆኑና ነዳጁ ሲቀዳ የሚቀዳው ብዛት በሊትር ደረሰኙ ላይ የማይገለጽ ከመሆኑ በተጨማሪ ዋጋው በጥቅል ብቻ የሚቀመጥ መሆኑ፤
- በአብዛኛው ደረሰኝ ላይ የአንድ ዋጋ የማይጠቀስ፣ ማህተም የሌለው፣ ቀን በትክክል የማይጻፍ መሆኑ፤
- በአብዛኛው ነዳጅ የቀዱበት ደረሰኝ ላይ የመኪና ታርጋ ቁጥር የማይጻፍ መሆኑ፤
- በተጨማሪም ኮድ 4-20211 ቶዮታ ሎንግ ቤዝ መኪና ብቻ በየቀኑ ነዳጅ እየተቀዳበት መሆኑ ታውቋል፡፡

[redacted]በቀን 12/04/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 1017552 የቱሪዝም ኢንቨስትመንት ስትራቴጂ ሰነዱን ለማዘጋጀት የመስክ ስራ ከአዲስ አበባ አዳማ የደርሶ መልስ አቶ ተመስገን ጌታቸው ሲሄዱ ከቀን 06/04/2014 እስከ 8/04/2014 ድረስ ለኮድ 4-24726 አንድ መኪና ላይ በየቀኑ ነዳጅ የተቀዳ መሆኑ፤

- መ/ቤቱ በበጀት አመቱ የተጓዙትን ኪሎ ሜትር ንባብ ከቀዱት ነዳጅ ጋር ሲናበብ መጠቀም ከነበረባቸው ነዳጅ በአግባቡ ለመጠቀማቸው የሚያሳይ ኖርማላይዜሽን (Normalization) የተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታን የሚያሳይ በተቋሙ ውስጥ ያልተዘጋጀ ወይም ያልተሰራ መሆኑን በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

4. <u>መሥሪያ ቤቱን ከለቀቁ ሠራተኞች የሚፈለጉ ቋሚ ንብረቶች</u>

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ከሚኒስትር መ/ቤቱ ከሥራ የለቀቁ ሶስት ሠራተኞች ይገለገሉበት የነበረውን ቋሚ ንብረት ሳያስረክቡ የለቀቁ መሆኑ፤

በተጨማሪም ሁለት ሰራተኞች የፕሮጀክት ሰራተኞች ናቸው በማለት ንብረት ሳያስረክቡ ከስራ የለቀቁ መሆኑ ታውቋል፡፡

የህግ ደንብና መመሪያ ጉዳዮች(Compliance Issue)

1.በባለሙያ ሳይረጋገጥ የተፈጸመ የላንድ ማርክ ግንባታ ወጪብ

ሰኔ 2002 የወጣው የግዥ መመሪያ አንቀጽ 28.5 ሀ ለግንባታ ስራ ክፍያ የሚፈጸመው የሥራውን ደረጃ ተከትሎ ከአማካሪ መሀንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መነሻነት ብቻ መሆኑ ይጠቅሳል ፡፡

ይሁን እንጂ ተቋሙ በተለያዩ ቦታዎች ለሚያስገነባቸው የላንድማርክ ግንባታዎች አማካሪ ድርጅቶችን በማወዳደር ስራው በሚገባ ስለመሰራቱና ስራው ባለበት ደረጃ እየተመዘነ የክፍያ ጥያቄዎች ሲደረሱ በአማካሪ ድርጅቱ እየተረጋገጠ መከፈሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፤

- በቀን 20/08/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 1247 በሂሳብ መደብ 224110 በኦሊራ ኮንስታራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ በበቆጂ ለሚገነባው የላንድ ማርክ ግንባታ ስራ የመጀመርያ ክፍያ ብር 452,093.01 የተከፈለ መሆኑ፤
- በቀን 23/08/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 1018 በሂሳብ መደብ 224110 በኦሊራ ኮንስታራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ በበቆጂ ለሚገነባው የላንድ ማርክ ግንባታ ስራ 20% ክፍያ ብር 167,039.00 የተከፈለ መሆኑ፤
- በቀን 23/08/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 1044 በሂሳብ መደብ 224110 ሃጃ ፊጅ ኮንስታራክሽን እና ኢንጅነሪግ ኃ/የተ/የግ/ማ በሐረር ከተማ ለሚገነባው የላንድ ማርክ ግንባታ ስራ የመጀመርያ ዙር ክፍያ ብር 279,599.18 የተከፈለ መሆኑ፤

በድምር ብር 898,731.19 ክፍያ ሲፈጸም ከአማካሪ መሐንዲስ ስራው ያለበትን ደረጃ እና የተሰራው ስራ ተረጋግጠ የቀረበ ማስረጃ ሳይኖር ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2. ያለውድድር የተፈፀመ ግዥ

በፌዴራል መንግስት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ 6 አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ መሠረት የመንግሥት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት ዕቃው፣የግንባታ ዘርፍ ስራው፣ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ነዉ ብሎ ይደነግጋል፡፡ ይሁን

እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ግዥዎችን በአዋጁ መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ለታላቁ ሩጫ ውድድር ዝግጅት በሚል ብር 1,927,495.01
- የተለያዩ የአገር ውስጥ ባህላዊ አልባሳት ግዥ ብር 958,289.03
- ከተለያዩ ሆቴሎች የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ብር 923,988.99
- ለማስታወቂያ አገልግሎት ግዥ ብር 211,968.00

በድምሩ ብር 4,021,741.03 ከመመሪያ ውጪ ያለውድድር በቀጥታ በማከናወን ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

3. በጨረታ መገዛት ሲገባው በመከፋፈል በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ

በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 33 ቁጥር 4 በዚህ አዋጅ ወይም በግዥ መመሪያው የተዘረጉ የግዥ ስርዓቶችን ለማሻሻል የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት መፈጸም የሚገባቸውን የእቃ፤ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን መከፋፈል የለባቸውም ይላል፡፡

ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሽከርካሪ ጎማ፤መለዋወጫ እና ጌጣጌጥ ግዥ በጨረታ መፈጸም ሲገባው በመከፋፈል በዋጋ ማወዳደሪያ የግዥ ዘዴ በተደጋጋሚ በማከናወን በድምሩ ብር 1,556,682.50 በመከፋፈል በዋጋ ማወዳደሪያ የግዥ ዘዴ በማከናወን ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

4. በተጋነነ ዋጋ የተፈፀመ የአልባሳት ግዥን በተመለከተ፤

የፌዴራል መንግስት የግዢ አፈፃፀም መመሪያ 2002 አንቀፅ16.19.3 በአሸናፊዉ ተጫራች ያቀረበዉ ዋጋ ጨረታዉ ከመዉጣቱ በፊት በመንግስት መ/ቤቱ ከተገመተዉ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር በከፍተኛ ልዩነት የሚበልጥ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ባለመሆኑ አዲስ ጨረታ ማዉጣት የሚሻል መሆኑ ሲታመንበት ድጋሚ ጨረታ ማዉጣት አስፈላጊ እንደሆነ ይገልፃል፡፡በተጨማሪም መ/ቤቱ ግንቦት /2014 ባወጣው የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎች፤ የደንብና የፕሮቶኮል አልባሳት አሰጣጥ እና አጠቃቀም መመሪያ መሰረት የደንብ ልብስ ግዥዎችን እየፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ለመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ 3 ሹፌሮች የፕሮቶኮል ልብስ አገልግሎት ማለትም፡-

- ሙሉ ልብስ የአንዱ ዋጋ ብር 32,500.00

- የሱፍ ጫማ የአንዱ ዋጋ ብር 13,500.00
- ሸሚዝ የአንዱ ዋጋ ብር 1,350.00
- ከረባት የአንዱ ዋጋ ብር 1,750.00
- ቀበቶ የአንዱ ዋጋ ብር 1,950
- ካልሲ የአንዱ ዋጋ ብር 450.00

በቀን 21/10/2014 በወጪ ማስመስከርያ ቁጥር 954 ብር 322,200.00 ከታሜጋስ ጀኔራል ትሬዲንግ በተጋነነ ዋጋ ግዥ በማከናወን ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

5. <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ፤</u>

በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 የተከፋይ ሂሳብ በአንቀጽ 8 ቁጥር 5 ከፊደል ሀ-ሠ በዝርዝር በተቀመጠው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ እየተከፈለና እየተመዘገበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በበጀት ዓመቱ የሂሳብ ሪፖርት ላይ በድምሩ ብር 540,930.64 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብን መኖሩ በኦዲት ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት